# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 54 ግንቦት 20 2001 ዓ.ም

**"ወያኔ በአገዛዝ ዘመኑ በተግባር እንዳስመሰከረው ጸረ አማራ; ኦሮሞ :ጉራጌ: ወላይታ: ከምባታ: አፋር: ሱማሌ : አኝዋክ ወዘተ ይሆናል ተብሎ ቢታሰብ ኖሮ ሌላው ቢቀር የወሎ : የጎንደር የጎጃምና የሰሜን ሸዋ ህዝብ በጉያው ውስጥ ደብቆ ከደደቢት አሰከ ሰሜን ሸዋ የሚዘልቀውን ጠመዝማዛ መንገድ እንዲጓዝና ምንሊክ ቤተመንግሥት ድረስ እንዲዘልቅ አይፈቅድለትም ነበር"**

**"በመከላከያ ውስጥ የሚገኙ 7 ቁለፍ ቦታዎች 6 መምሪያዎችና የኤታማዦር ሹምነቱን ጨምሮ በሙሉ የተያዙት በትግሬዎች ነው"**

**"በስራ ላይ ከሚገኙት 39 ጄነራሎች መሃል 28ቱ ትግሬዎች ሲሆኑ 5 ኦሮሞ 4 አገው እና 2 አማሮች ይገኙበታል"**

**ሃይለ ቃል**

## ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ በአውሮፓ ከተማዎች እየተዘዋወሩ ህዝባዊ ስብሰባዎችን ማድረግ እና ባለስልጣናትን ማናገራቸውን ቀጥለዋል

የግንቦት 7 የፍትህ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ መሪ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ በተለያዩ የአውሮፓ ከተማዎች እየተዘዋወሩ ህዝባዊ ስብሰባዎችን ማድረግ እና ባለስልጣናትን ማናገራቸውን ቀጥለዋል። ባለፈው ቅዳሜ በጀርመን አገር፤ እና እሁድ በስዊዘርላንድ ስብሰባዎችን አድርገዋል።

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በተለያዩ የአውሮፓ አገራት ላሉ ኢትዮጵያዉያን የግንቦት 7ን አላማ ለማስረዳት እና ለድርጅቱ የገንዘብ እና የማቴሪያል ድጋፍ ለማሰባሰብ በስዊዲንና በኖርወይ ከአገራቱ ባለስልጣናት ጋር እንደተውያዮና ከኢትዮጵያውያን ጋር ስብሰባ እንዳደረጉ እንዲሁም በበልጄም ብራስልስ ካውሮፓ ህብረት ባላስልጣናት ጋር ውይይት ማድረጋቸውን መዘገባችን ይታወሳል።

ዶ/ር ብርሃኑ የስራ ጉኝታቸውን በመቀጠል ባለፈው ቅዳሜ ግንቦት 15 ቀን በጀርመን አገር ፍራንክፈርት ከተማ ባደረጉት ስብሰባ፣ ምንም እንኳ ስብሰባው የሚጀመረው ከቀኑ ሰባት ሰዓት መሆኑ ቢነገርም ከበርካታ የጀርመን ከተሞች በመጉረፍ የመጡት ኢትዮጵያውያን ከጠዋት ጀምረው በስብሰባው አዳራሽ መጠባበቅ መጀመራቸውን ዘጋቢያችን ከስፍራው ከላከልን ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል። በዚህ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በተገኙበት ስብሰባ ላይ፣ ዶ/ር ብርሃኑ በአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ላይ እና በህብረት ትግል አስፈላጊነት ላይ ንግግር ያደረጉ ሲሆን፣ ባጠቃላይ ስድስት ሰዓት የፈጀ ውይይት መደረጉ ተዘግቧል።

በእለቱ ከስብሰባው አዘጋጆች አንዱ ለዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የኢትዮጵያን ባንዲራ በመስጠት፥ "በወያኔ የተረገጠችውንና የተጣለችውን የአንድነትና የህብረታችን መገለጫ የሆነችውን ሰንደቃላማችንን፣ ትግሉን በወኔ ሙሉነት መርተውና አታግለው ያነሷትና ያስከብሯት ዘንድ፣ እንደ ቀድሞው ሁሉ ከፍ ብላ እንድትውለበለብ ያደርጉ ዘንድ አደራ" በማለት እንዳበረከቱላቸው ታውቋል። ዶ/ር ብርሃኑም፥ የባንዲራ አደራ ቀላል እንዳልሆነና የተሰጣቸውን አደራ በተግባር መወጣት እንዲችሉ የኢትዮጵያውያን ድጋፍ እንደሚያስፈልግ በማስገንዘብ መቀበላቸውን ዘጋቢያችን ጨምሮ ጠቅሷል። (**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**)

## በመፈንቅለ መንግሥት ወንጀል ሰበብ በእስር ያጎራቸውን ዜጎች በማንም እንዳይጎበኙ አልከለከልኩም የሚለው የውያኔ የአደባባይ ቅጥፈት የእስረኞቹ ቤተሰቦች ሃሰት ነው ሲሉ አጋለጡ።

ወያኔ በመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ወንጀል ስብስቦ በእስር ቤት ያጎራቸውን እስረኞች በማንም እንዳይጎበኙ አልተከለከሉም በማለት ሽመልስ ከማል ከትናንትና በስቲያ ለቪኦኤ የሰጠውን የአደባባይ ላይ ቅጥፈት የእስረኞቹ ቤተሰቦች ሃሰት ነው ሲሉ አጋለጡ።

ሰብዕና የጎደላቸውን ሰዎች ዳጎስ ባለ የገንዘብና የሹመት ጥቅም ደልሎ በዙሪያው ያሰለፈው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም በህዝባችን ላይ የሚፈጽመውን ሰቆቃ በአደባባይ ላይ ወጥቶ ከሚያስተባብሉለት አንዱ የሆነው ሽመልስ ከማል ባለፈው ማክሰኞ ግንቦት 18 ቀን ለአሜሪካ ድምጽ የእንግሊዘኛ ክፍል በሰጠው ቃል በመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ውንጀላ የተከሰሱ ሰዎች እንዳይጎበኙ አልተከለከሉም ማለቱ የሚታወስ ነው።

ይህንን የሰሙ የእስረኞች ቤተሰብ ለቪኦኤ የአማሪኛው ክፍል ባልደረባ ለእስክንድር ነጋ ትናንት ግንቦት 19 በሰጡት ቃል፣ እስረኞቹ ከታሰሩበት የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ በየቀኑ ከአንዴም ሁለቴ እየተመላለሱና ከእስርቤቱ ባለስልጣኖች አልፈው ለበላይ አለቆቻቸው አቤት ብለው ሰሚ እንዳላገኙ፤ ይልቁንም ይህ የሙብት ረገጣ አልበቃ ብሎ የኮሚንኬሽን ኤጀንሲ ምክትል ዴታ የሆነው ሽመልስ ከማል (**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**)

## በግንቦት 7 ንቅናቄ የተደናበረው የወያኔ አገዛዝ ጎረቤት አገር በስደት የሚገኙትን ሳይቀር መወንጀል ጀምሮአል

"መፈንቅለ መንግስት ሊደረግብኝ ነበር" ካለ በኋላ በተለይ፤ እንደቆሰለ አውሬ በየቦታው እየተቅበዘበዘ ንጹሀን ዜጎችን በሀገር ውስጥ ማደን አልበቃ ብሎት ዘረኛው ወያኔ በጎረቤት ሀገራት በስደት የሚኖሩ ኢትዮድያዊያንን ለማጥቃት ማቀዱን የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል። እንደውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ገለጻ፥ ወያኔ በዩጋንዳ የሚኖሩ በግንቦት ሰባት አደራጅነት እና አባልነት የጠረጠራቸው ሰዎች ቤት እንዲፈተሽ እና ተላልፈው እንዲሰጡት ለዩጋንዳ መንግስት ጥያቄ አቅርቧል።

የዩጋንዳን የጸጥታ ሀላፊዎች ዋቢ አድርገው ዜናውን ያደረሱን ምንጮቻችን የዩጋንዳ መንግስት የወያኔን ኡኡታ ከቁም ነገር እንዳልቆጠረው ታውቋል። ከወራት በፊት ተሰፋዬ የተባለ ወያኔን ተክቶ በዩጋንዳ የኢትዮድያ ኤምባሲ አንደኛ ጸሀፊ የሆነው ግርማ ተክለጽዮን ጥያቄውን እንዳቀረበ ተዘግቧል። አዲስ አበባ በህዝብ ላይ ተዘርዝሮ የማያልቅ ግፍ የሚፈጽሙ ሰላዩች እና ደህንነቶች ሀላፊ የነበረው ግርማ በቅርቡ ለዚሁ ጉዳይ ከሀገር ቤት ከመጡ የወያኔ ልኡካን ጋር አብሮ 'ግንቦት ሰባት በካምፓላ አፍሪካን የሚያስተባብርበት ጽህፈት ቤት አለው፤ አባላቱ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የጦር መሳሪያ ደብቀዋል እና ቤታቸው ይፈተሽልኝ' የሚል ክስ እንዳቀረበ ተመልክቷል። ስደተኞቹ ምንም አይነት መሳሪያ እንደደበቁ የሚያሳይ መረጃ እንደሌለው የገለጻው የዩጋንዳ የደህንነት ክፍል የወያኔን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉን ታውቋል።

የውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ያነጋገሯቸው የወያኔን እመቃ አምልጠው በስደት ዩጋንዳ የሚኖሩ ኢትዮድያዊያን ጉዳዩን በቅርበት እንደሚያውቁት እና፤ ወያኔ ተላልፈው ይሰጡኝ፣ ቤታቸው ይፈተሽልኝ ማለቱ የሚያስጨንቃቸው ጉዳይ እንዳልሆነ ገልጸዋል። ዘጋቢያችን የነጋገራቸው አንድ ደተኛ፣ "የሚያስጨንቀን ጉዳይ ወያኔ በግፍ በየእስር ቤቱ የሚያሰቃያቸው እና ሰቆቃ የሚፈጽምባቸው ወገኖቻችን ስቃይ ነው" ሲሉ ገልጸዋል (**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**)

## የኢህአዴግ አባል ያልሆኑ መንግስት ሰራተኞች በብቃት ማነስ ስም ከስራ ሲባረሩ የጡረታ አበል ለማግኘት እንዳይችሉ አስቸጋሪ የሚያደርግባቸው ህግ በወያኔ ፓርላማ ጸደቀ።

የመለስ አገዛዝ መንግስት ሰራተኞች የጡረታ አበል ማግኘት የሚችሉበትን ጊዜ ከፍ የሚያደርግ ረቂቅ አዋጅ ለፓርላማ ተብዬው ማቅረቡን ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል። ቀድሞ በነበረው ህግ መሰረት የመንግስት ሰራተኞች የ20 አመት አገልግሎት ከሰጡ እና 45 ዓመት ከሞላቸው የጡረታ አበል መቀበል እንደሚችሉ ይታወቃል።

ማክሰኞች፣ ግንቦት 18 ቀን በወያኔ ፓርላማ ያለምንም መሻሻል የጸደቀው አዲስ አዋጅ የመንግስት ሰራተኞች የጡረታ አበል ለማግኘት 25 አመት ያገለገሉና 50 ዓመት ሊሆናቸው እንደሚገባ ይደነግጋል። አገዛዙ ይህንን ድንጋጌ ያወጣበትን ምክንያት ሲገልጽ በጡረታ ፈንድ ላይ የሚፈጠረውን ጫና ለመቀነስ ነው ማለቱ ይታወሳል። ነገር ግን፥ ጉዳዩን በሚመለከት ያነጋገርናቸው አስተያየት ሰጪዎች፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አገዛዙ በብቃት ማነስ ስም የኢህአዴግ አባላት ያልሆኑ የመንግስት ሰራተኞችን በብዛት እያባረረ ስለሆነ፣ ተጨማሪ ቅጣት ለመስጠት መሆኑ ጥርጣሬ እንደሌለው ተናግረዋል።

የረቂቅ አዋጁን ተመልክቶ የውሳኔ ሃሳብ ለፓርላማ ተብዬው ያቀረበው፣ በሙስና ባፈራችው ሃብት ዝናን ባተረፈችው እና የአምባገነኑ መለስ ሚስት በሆነችው አዜብ መስፍን የሚመራው የማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መሆኑ ተዘግቧል።

በተያያዘ ዜና፥ የመለስ አገዛዝ ባለስልጣናቱ ከስራቸው ቢነሱ የሚያገኟቸውን ጥቅሞች በተመለከተ ለፓርላማ ተብዬው ግንቦት 13 ቀን 2001 ዓም ረቂቅ አዋጅ ማቅረቡ ታውቋል። በዚህ ረቂቅ አዋጅ መሰረት መለስ ዜናዊ ከስልጣኑ ቢወርድ፥ አሁን የሚከፈለው ደሞዝ እና አበል እስከለተ ሞቱ የማይቋረጥ ሲሆን፣ ስልጣን ላይ ላለው አቻው ደሞዝ ሲጨመርለት ለመለስም ይጨመርለታል።

በተጨማሪም፥ ባለብዙ መኝታ ክፍል ቤት፣ እና የሾፌሮቻቸው ደሞዝ እና ሌላ ወጪዎች ሙሉ በሙሉ በመንግስት የሚሸፈን ደረጃቸውን የጠበቁ ሶስት መኪናዎች የሚሰጡት ሲሆን፤ እሱ ወይም የቤተሰቡ አባል ሲታመሙ አገር ውስጥም ሆነ ውጭ አገር የሚታከሙበትን ወጪ መንግስት የሚሸፍነው መንግስት ይሆናል። (**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**)

## ዘረኝነትን መግላገል ለዛሬ ያደረ የትናንት የቤት ሥራችን!!!

ኢትዮጵያችን ኋላ ቀር ፊውዳላዊና ጨቋኝ ስርአት ስታዘግም ኖራ ወደ ወታደራዊ አምባገነን ከዚያም ወደ ጎጠኛ አምባገነን ስትሸጋገር ከረመች። ከትናንት ወዲያ ኢፍተሃዊነትና ብዝበዛ ያንገፈገፈው የኢትዮጵያ ህዝብ የአጼውን ፊውዳላዊ ስርአት በትግሉ አሽቀንጥሮ ሲጥለው ድሉን ግን በተቧደኑ ወታደሮች ተቀማና አምባገነንነት ሰፈነ ። በዚያን ወቅት ሥልጣን የህዝብ ይሁን ያሉና የህዝቡን እሮሮ ሲያስተጋቡ የነበሩ ውድ ልጆቹ ያለምንም ርህራሄ ደርግ በጥይት አረር ቆላቸውና የኢትዮጵያ ጎዳናዎች በደም ጎርፍ ታጠቡ። የዚያ ቁስል የፈጠረው ምሬትና ጥላቻ ውሎ አድሮ ከዚያ ሁሉ ሰራዊት አቅም በላይ ሆነና ደርግን ለከርሰ መቃብር ዳረገው። በነመንግሥቱ ኋይለማሪያም ቀጭን ወታደራዊ ት'ዕዛዝ የገዛ ወንድሞቹን በጥይት ሲቆላ የነበረ የመከላኪያ ፤ የፖሊስና የደህንነት ተቋማቱም እንደተቋም እንኳ መቀጠል የሚያስችለውን አቅም አጡና በውስጡ የነብሩ የወንጀሉ ተባባሪዎችም ሆኑ ንጹሃን በጅምላ የመብተን እጣ ፈንታ ገጠማቸው።

ታሪክን መለስ ብለን ስንቃኝ የአጼውን ሥርዓት የተቃወሙት ለጭሰኝነት ከተዳረጉት አፈር ገፊ ወላጆች የተወለዱ ብቻ ሳይሆኑ በወላጆቻቸው የመደብ ጀርባ ተጠቃሚ የነበሩ የመኳንንቱ፡ የመሳፍንቱና የባላባቶች ልጆችም ጭምር ስለነበሩ በኢፍትሃዊነትና በጭቆና ላይ በጋራ መዝመት ደርግ ወደከርሰ መቃብሩ እስከወረደበት ጊዜ ድረስ የዘለቀ ብቻ ሳይሆን በአገራችን ፍትህና እኩልነት እስከሰፍን የሚዘልቅ እሴታችን ሆኖ ቆየ ፡፡ እንዲህ አንደዛሬ ከዘመናዊ ትምህርት የሚቀሰም ትምህርት ባልነበረበት በዚያ የጨለማ ዘመን አባቶቻችን በመካከላቸው ከነበረው የዘውግና የሃይማኖት ልዩነት በላይ ሆነው በአጥንታቸው ፍርስራሽ ያቆዩልንን ነጻ አገር ለሁላችንም የእኩል ቤት ማድረግ አለመቻል ምንኛ አለምታደል ነው?

የአጼው ሥርዓት ሲያከትም ደርግ ከአጼው ይሻላል ብለው ተስፋ አድርገው ነበር። የደርግ ሥርዓት ሲደረመስ እርሱን ተክተው ሚኒልክ ቤተ መንግስት የገቡትን ተረኞች ማንም ከደርግ ይከፋሉ ብሎ አልጠበቀም ነበር። በዘውጉ ስም እየማሉ ሲገዙቱ ማንም ዛሬ ያለውን አይነት ዘረኝነት በኢትዮጵያ ያሰፍናሉ ብሎ አልጠበቀም። ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ዘረኝነት እጅግ ያፈጠጠ እንደሆነ በመግለጽ ሁላችንም ይህን እውነት የመጋፈጥ ወኔ ሊኖረን ይገባል ብለን ተማጽነናል። ያንን ለመጋፈጥ የሚሆን ወኔ ከድቶን በዝምታ ብናልፈው በታሪክ የሚያስወቅሰን እጅግ አደገኛ የሆነ መዘዝ የሚያስከትል እንደሆነ ገልጸን አስጠንቅቀናል። ተማጽኖአችን ሆነ ማስጠንቀቂያችን በተራ አሉባልታ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን እጅግ በሚጎመዝዝ መስረጃ ላይ የተደፈ እንደሆነ ሰሚ ጆሮ ላለው ሁሉ አሰምተናል።

ይባስ ብሎ አሁን አሁን ደግሞ በደህንነቱና በፖሊስ አካባቢ እጅግ ዘግናኝ የሆነ ዘረኛ መዋቅር መዘርጋቱን የሚያሳዩ መረጃዎች እየደረሱን ነው። በኢኮኖሚው መስክም እንዲሁ የተንሰራፋው የዘረፋ መዋቅር እጅግ ዘግናኝ ነው። በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ያለው የሥልጣን ክፍፍል ምን እንደሚመስል ይፋ እንድናደርግ ካስገደዱን ምክንያቶች አንዱ ዘረኝነት ለማናችንም ስለማይበጅ ሊቆም ይገባል ብለው ጥያቄ ያነሱ ወገኖቻችን በመንግስት ግልበጣ ተወንጅለው ዘብ ጥያ ከወረዱ ወዲህ እጅግ አሰቃቂ ፍዳ እያዩ እንደሆነና መረጃ ስለደረሱን ነው። እነዚህ ወገኖቻችን በድብደባ ብዛት ሰውነታቸው እጅግ ከመተልተሉ የተነሳ ዘመድ አዝማድ እንዳያያቸው ተደርገው በተሸፋፈኑ ካሚዮኖች ጭነው ከማሰቃያ ማዕከላት ፍርድ ቤት እያመላለሱአቸው እንደሆነ ዓለም በትካዜ እየሰማ ነው።

እንዲህ ዓይነቱን ዘረኝነትን ማንም ሰብአዊ ፍጥረት ሊቀበለው አይቻለውም። በአንድ ሀገር ውስጥ አንዳችን የበታች ሌላችን የበላይ ሆነን የምንኖርባትን እውነታ በጸጋ ተቀብለን ለመኖር ፈጽሞ አንሻም። ትግሬው ይህን ተቀብሎ፣ ህሊናው አርፎ ሊኖር አይችልም። የአገው ሰው፣ ኦሮሞው፣ ጉራጌው፣ ሽካውና አማራው እጅግ ያንገፈግፋቸዋል። ለዚህ ነው ዘረኝነትን መታገል የሁላችንም እዳ ነው የምንለው። ለማንም ሊተው የማይገባው እዳ። ትናንት መከፈል ሲገባው ለዛሬ ያደረ እዳ። ትናንት ልንገላገለው ሲገባ ዛሬም ያልተገላገልነው በሃይል የተጫነብን ቀንበር። ይህ እዳ የአማራው፣ የሶማሌው፣ የአፋሩ፣ እዳ ነው። ይህ ቀንበር የትግሬው፣ የኦሮሞው፣የሱርማው፣ የሲዳማው ነው። ይህ ሸክም የጋምቤላው የደራሼው የከፋው የከንባታው፣ የሃዲያው ሸክም ነው። ትናንት ከትናንት ወዲያ ልናራግፈው ልንገላገለው ሲገባን ለዛሬ ያደረ ሸክም፣ ቀንበርና እዳ። ትናንትና ከዚያ በፊት መስራት ሲገባን ሳይሰራ ለዛሬ ያደረ የቤት ሥራ!!!

### በመፈንቅለ መንግሥት ወንጀል ሰበብ በእስር ያጎራቸውን ዜጎች በማንም እንዳይጎበኙ አልከለከልኩም የሚለው የውያኔ የአደባባይ ቅጥፈት

(ከገጽ 1 የዞረ)

“አንድም የቤተሰብ አባል እስረኞቹን ልጠይቅ ብሎ ጥያቄ ያቀረበ የለም” ብሎ በአደባባይ የሰጠው ቅጥፈት እጅግ እንዳሳዘናቸው በምሬት ገልጸዋል።የማያሳፍራቸው ተግባር መሆኑን የማያውቅ የለም።

የመለስ ዘረኛ ቡድን በህዝባችን ላይ የሚፈጽመው ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ፣ አፈናና ሰቆቃ ለማስተባበል ቅንጣት ታህል የሞራልና የሃይማኖት እሴት ግድ ከማይላቸው አንዱ የሆነው ሽመልስ ከማል፣ በድህረ ምርጫ 97 በአዲስ አበባና ሌሎች ከተሞች ለተጨፈጨፉ ወገኖቻችን ቅንጅትን ተጠያቂ ለማድረግ ወያኔ ባቋቋመው አሻንጉሊት ፍርድ ቤት ክስ ለመመስረት ከሳሽ ሆኖ የሚቀርብ አቃቤ ህግ በታጣበት ወቅት በሃላፊነት ይመራ ከነበረው የኢትዮጵያ ብሮዲካስቲንግ ኤጀንሲ ሥራው ላይ በተደራቢነት ለመስራት በፍቃደኝነት የቀረበ አድር ባይ ሰው እንደሆነ በቅርበት የሚያውቁት የሙያ ባልደረቦቹ ይናገራሉ።

“ውሸት ከመናገር እውነቱን ተናግሮ የመሸበት ማደር” የሚል ከፍተኛ የሞራልና የባህል እሴት ባለው ህዝባችን ውስጥ ለሆዳቸው ጥቅም ከወያኔ በሚያገኙት ፍርፋሪ ተደልለው እንዲህ አይነት ህዝብ ያወቀው ጸሃይ የሞቀውን ሃቅ ለማድበስበስ የተቀመጡበት የመንግሥት ስልጣን መቀመጫ የማይከነክናቸው ሰዎች፣ ወጣቱን ትውልድ እንዳይበክሉትና በሰው ልጆች ግንኙነት መካከል መሰረት የሆነውን እውነት የመናገር ባህልን እንዳይበርዙት ብዙዎች ስጋት አላቸው። ወያኔ ሥልጣን ከያዘበት ዘመን ጀምሮ በሙስና መከበርና የወያኔን እድሜ ለማራዘም አስከሰራ ድረስ በስልጣን ላይ ያሉት ሁሉ በአደባባይ ሙልጭ ያለ ውሸት መናገር

### የኢህአዴግ አባል ያልሆኑ መንግስት ሰራተኞች በብቃት ማነስ ስም ከስራ ሲባረሩ የጡረታ አበል ለማግኘት እንዳይችሉ አስቸጋሪ የሚያደርግባቸው ህግ በወያኔ ፓርላማ ጸደቀ። (ከገጽ 1 የዞረ)

ይህንን በተመለከተ ያነጋገርናቸው የፖለቲካ ተንታኝ፥ “መለስ ይህንን ረቂቅ አዋጅ ይዞ የተነሳበት ብዙ ፖለቲካዊ ምክንያቶች አሉ፤ ነገር ግን እነሱን እንኳ ትተን የተነገረንን ብቻ ብንወስድ፤ በኢትዮጵያ ካለው ብልሹ ስርዓት የተነሳ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች በያመቱ የእርዳታ ጥገኞች ሆነው ባሉበት አገር፤ እንዲሁም በገንዘብ እጥረት ስም የብዙሃኑ መንግስት ሰራተኞች የጡረታ መብት እየተገደበ ባለበት፤ መለስ ዜናዊ ከድብቅ ዘረፋው አልፎ እንደዚህ አይን ባወጣ ሁኔታ ይህ ሁሉ ገንዘብ እና ይህ ሁሉ መኪና ይሰጠኝ ብሎ መጠየቁ ማን አለብኝነቱ እና ጥጋቡ የደረሰበትን ከፍተኛ ደረጃ ያሳያል” ብለዋል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

# በመከላከያ ሰራዊ ውስጥ ባሉ ቁልፍ የአዛዥነት ቦታዎች ላይ የሚገኙ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች የብሄረሰብ ተዋጽኦ

በዘረኝነት ላይ የተመሰረተው የወያኔ አገዛዝ በውስጡ ባሰባሰባቸው ጥቂት ፀረ አገርና ጸረ ህዝብ ሃይሎች ላለፉት 18 አመታት የፈጸማቸው ወንጀሎች በአገሪቷ ታሪክ ታይተው የማይታወቁ መሆናቸው ተብሎ ያለቀለት ነገር ነው። በማንኛውም አገር ያልተለመደ ይልቁንም የአውሮጳ ቅኝ ገዥዎች ቅኝ በገዙዋቸው አገሮች ይፈጸሙት የነበረው አይነት ግፍና መከራ በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ለመሆኑ ለኢትዮጵያዊያን መግለጽ ለቀባሪ ማርዳት ነው፡

ወያኔ ወደ ስልጣን በመጣ ማግስት ጀምሮ የአገሪቱን ሃብት አይን ባወጣ መንገድ መዝብሯል፡; የንግድና የኢኮኖሚ ተቋማቱን ፍጹም ይሉኝታ በሌለውና በአገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ለአፍራሽ አላማ ከአንድ ዘውግ በተሰባሰቡ የጥቅም ሽሪኮች እጅ እንዲገባ አድርጓል፡ ለመብታቸው መከበር የተነሱትን ዜጎች ለመደፍጠጥ ከደርግ በከፉ ፋሽስታዊ ጭካኔ ጨፍጭፏል።

በ17 ዓመታቱ የደርግ ኮሚንስታዊ አስተዳደር የተማረረው አብዛኛው የአገራችን ህዝብ ጸረ ደርግ ትግል አካሂዳለው ይል የነበረን ወያኔን አቅፎና ደግፎ ለድል ያበቀበት ዋናው ምክንያት የወያኔን መሪዎች አገራዊ አጀንዳ አላቸው ብሎ በማመኑ እንደነበር የግንቦት 7 ንቅናቄ ያምናል:: ግንቦት 7 በኢትዮጵያ ላይ በተደጋጋሚ ተቃጥቶ የነበረን የውጭ ወረራ ከሌሎች ወንድሞቹ ጋር ሲመክት ከኖረው ጀግናው የትግራይ ህዝብ አብራክ እንደ መለስ ዜናዊና ጥቂት ግብረአበሮቹ ያሉ ከሃዲዎች ይፈጠራሉ ብሎ ለማመን ይቸገራል። ወያኔ በአገዛዝ ዘመኑ በተግባር እንዳስመሰከረው ጸረ አማራ; ኦሮሞ :ጉራጌ: ወላይታ: ከምባታ: አፋር: ሱማሌ : አኝዋክ ወዘተ ይሆናል ተብሎ ቢታሰብ ኖሮ ሌላው ቢቀር የወሎ : የጎንደር የጎጃምና የሰሜን ሸዋ ህዝብ በጉያው ውስጥ ደብቆ ከደደቢት እስከ ሰሜን ሸዋ የሚዘልቀውን ጠመዝማዛ መንገድ እንዲጓዝና ምንሊክ ቤተመንግሥት ድረስ እንዲዘልቅ አይፈቅድለትም ነበር። የተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ የትግራይን ህዝብ እንደሌሎች ህዝቦች በወንድምነትና በእህትነት በመመልከትና ከአካባቢው የተነሳውን ትግል እንደራሱ ትግል አድረጎ በመውሰድ ወያኔ የጀመረው ትግል ዳር እንዲደርስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ወያኔ ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ያደረገለትን ውለታ በመዘንጋት ዋና ዋና የሚባሉትን የመከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ የአዛዥነት ስልጣን ቦታዎችን ከአንድ ጎጥ በመጡ ሰዎች አስይዟል። ይህን የሚያደርገውም ሌላውን የኢትዮጵአ ህዝብ በመናቁ፣ በመጥላቱና በመፍራቱ መሆኑን መግለጽ ያሻል።

ምንም እንኳ ወያኔ እነዚህን ቁልፍ የስልጣን ቦታዎች በጎጡ ልጆች እንዲያዙ ቢያደርግም፣ ከአፓርታይድ አገዛዝና ከሌሎችም ተሞክሮዎች እንደታየው፣ በዘር ላይ የተመሰረተ አገዛዝ ረጅም እርቀት መጓዝ አለመቻሉን ነው። በዘር ላይ ተመስርተው የነበሩ አገዛዞች አወዳደቃቸው እንደላማረ ሁሉ የወያኔ የመጨረሻ ውድቀትም ከእነሱ የከፋ እንጅ የተሻለ እንደማይሆን ግንቦት 7 ያምናል።

የተከበርከው የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ፣ በጠባብ የጥቅም ዓላማ ከእንድ ጎጥ በመጡ ሰዎች ፍጽም ጭካኔ በተሞላው አኳሀን እየተገዛህ መሆንክህን ለማሳየት ከመከላከያ ያገኘነውን መረጃ እንደሚከተለው አቅርበንልሀልና ፍርዱን አንተው እንደትሰጥ እንጠይቃለን። የትግራይ ተወላጅ የሆናችሁትን ጨምሮ በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ያለሄውም ወገናችን በዘረኝነት ላይ የተመሰረተውን ይህንን ፍጹም አድል'ኦ በመቃወም ለፍትህ ለ'እኩልነትና ለዲሞክራሲ የምናደርገውን ትግል ትደግፍ ዘንድ ወቅቱ አደራ ይልሃልና ይህን መረጃ ተመልከተህ ውሳኔህን በአስቸኳይ እንድትሰጥም እንጠይቃለን።

## በመከላከያ ሰራዊ ውስጥ ባሉ ቁልፍ የአዛዥነት ቦታዎች ላይ የሚገኙ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች የብሄረሰብ ተዋጽኦ

### የመከላከያ ዋና መምሪያዎች

| ተራ ቁ | የስራ ምድብ | ማእረግ | ስም | ዘውግ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ጠቅ/ኤታማዦር ሹም | ጀኔራል | ሳሞራ የኑስ | ትግሬ |
| 2 | ስልጠና ዋና መምሪያ | ሌ/ጅኔራል | ታደሰ ወረደ | ትግሬ |
| 3 | ሎጂስቲክ ዋና | ሌ/ጅኔራል | ገዛኢ አበራ | ትግሬ |
| 4 | መረጃ ውና መምሪያ | ብ/ጅኔራል | ገብረዴላ | ትግሬ |
| 5 | ዘመቻ ዋና መምሪያ | ሜ/ጅኔራል | ገ/እግዜብሄር | ትግሬ |
| 6 | መሃንዲስ ዋና መምሪያ | ሌ/ጅኔራል | ብርሃነ ነጋሽ | ትግሬ |
| 7 | አየር ሃይል አዛዥ | ብ/ጅኔራል | ሞላ ኃ/ማሪያም | ትግሬ |

### እዝ አዛዦች

| ተራ ቁ | የስራ ምድብ | ወታደራዊ ማእረግ | ስም | ዘውግ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ማእከላዊ እዝ | ሌ/ጀኔራል | አበባው ታደሰ | አገው |
| 2 | ሰሜን እዝ | ሌ/ጅኔራል | ሳረ መኮንን | ትግሬ |
| 3 | ደቡብ ምስራቅ እዝ | ሜ/ጅኔራል | አብርሃ ወ/ገ/ለ | ትግሬ |
| 4 | ምእራብ እዝ | ብ/ጅኔራል | ስዩም ሃጎስ | ትግሬ |

### ክፍል ጦር አዛዦችማእከላዊ እዝ

| ተራ ቁ | የስራ ምድብ | ወታደራዊ ማእረግ | ስም | ዘውግ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 31ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ፀጋዬ ማርክስ | ትግሬ |
| 2 | 33ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ኪዳኔ | ትግሬ |
| 3 | 35ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ምስገናው አለሙ | አገው |
| 4 | 24ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ወርቅአይኑ | ትግሬ |
| 5 | 22ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ድኩል | ትግሬ |
| 6 | 8ኛ ሜ/ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ጀማል መሃመድ | ትግሬ |

### ሰሜን እዝ

| ተራ ቁ | የስራ ምድብ | ወታደራዊ ማእረግ | ስም | ዘውግ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 14ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ወዲ አንጥሩ | ትግሬ |
| 2 | 21ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ጉእሺ ገብሬ | ትግሬ |
| 3 | 11ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ወርቂዱ | ትግሬ |
| 4 | 25ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ተስፋይ ሳህል | ትግሬ |
| 5 | 20ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ተክላይ ክላሽን | ትግሬ |
| 6 | 4ኛ ሜ/ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ህንጻው/ጊዮርጊስ | ትግሬ |

### ደቡብ ምስራቅ እዝ

| ተራ ቁ | የስራ ምድብ | ወታደራዊ ማእረግ | ስም | ዘውግ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 19ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ወዲ ጉአኤ | ትግሬ |
| 2 | 44ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ዘውዱ ተፈራ | አገው |
| 3 | 13ኘ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ሽሪፎ | ትግሬ |
| 4 | 12ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ሙሉጌታ ብረሀ | ትግሬ |
| 5 | 32ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | አብርሃ ጸሊም | ትግሬ |
| 6 | 6ኛ ሜ/ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ገ/መድህን ፈቃደ | ትግሬ |

### ምእራብ እዝ

| ተራ ቁ | የስራ ምድብ | ወታደራዊ ማእረግ | ስም | ዘውግ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 23ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ወልደ ብእላሎም | ትግሬ |
| 2 | 43ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ወዲ አባተ | ትግሬ |
| 3 | 26ኛ ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | መብራቱ | ትግሬ |
| 4 | 7ኛ ሜ/ክ/ጦር አዛዥ | ኮ/ል | ገብረ ገ/ማርያም | ትግሬ |

### የመከላከያ ልዩ መምሪያዎች

| ተራ ቁ | የስራ ምድብ | ወታደራዊ ማእረግ | ስም | ዘውግ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አግአዚ ኮማንዶ ክ/ጦር አዛዠ | ብ/ጄ | መሃመድ ኢሻ | ትግሬ |
| 2 | አ/አ ዙሪያ ጥበቃ ክ/ጦር አዛዠ | ኮ/ል | ዘነበ አማረ | ትግሬ |
| 3 | ቤተ መንግስት ጥበቃ ሃላፊ | ኮ/ል | ገረንሳይ | ትግሬ |
| 4 | የባንኮች ጥበቃ ሃላፊ | ኮ/ል | ሃዋዝ ወልዱ | ትግሬ |
| 5 | ኤንጂኔሪንግ ኮሌጅ አዛዥ | ኮ/ል | ሃለፎም እጅጉ | ትግሬ |
| 6 | ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አዛዥ | ብ/ጄ | ተስፋይ ግደይ | ትግሬ |
| 7 | ሙሉጌታ ቡሌ ቴክኒክ ኮሌጅ አዛዥ | ኮ/ል | መለያ አማረ | ትግሬ |
| 8 | ሪሶርስ ማኔጅመንት ኮሌጅ አዛዥ | ኮ/ል | ለታይ | ትግሬ |
| 9 | ስታፍና ኮማንድ ኮሌጅ | ብ/ጄ | ሞግስ ሃይለ | ትግሬ |
| 10 | ብላቴን ማሰልጠኛ ማእከል | ኮ/ል | ሳልህ በሪሁ | ትግሬ |
| 11 | ውርሶ ማሰልጠኛ ማእከል | ኮ/ል | ነጋሽ ህሉፍ | ትግሬ |
| 12 | አዋሽ አርባ ማሰልጠኛ ማእከል | ኮ/ል | ሙዜ | ትግሬ |
| 13 | ብር ሸለቆ ማሰልጠኛ ማእከል | ኮ/ል | ነጋሲ ሽኮርተት | ትግሬ |
| 14 | መከላከያ አስተዳደር መምሪያ ሃላፊ | ብ/ጄ | መሃሪ ዘውዴ | ትግሬ |
| 15 | መከላከያ ደጀን አቬሽን ሃላፊ | ብ/ጄ | ክንፈ ዳኘው | ትግሬ |
| 16 | መከላከያ ጥናትና ምርምር ሃላፊ | ብ/ጄ | ሃለፎም ቸንቶ | ትግሬ |
| 17 | መከላከያ ፍትህ መምሪያ ሃላፊ | ኮ/ል | አስካለ | ትግሬ |
| 18 | ኤታ/ሹም ጽ/ቤት ሃላፊ | ኮ/ል | ጸሃየ ማንጁስ | ትግሬ |
| 19 | ኢንዶክትሪኔሽን ማእከል ሃላፊ | ብ/ጄ | አከለ አሳየ | አማራ |
| 20 | መገናኛ መምሪያ ሃላፊ | ኮ/ል | ስብሃት | ትግሬ |
| 21 | ውጭ ግንኙነት መምሪያ ሃላፊ | ኮ/ል | ሃሰነ | አማራ |
| 22 | ልዩ ሃይሎች ማስተባበሪያ ማእከል ሃላፊ | ብ/ጄ | ፍስሃ ማንጁስ | ትግሬ |
| 23 | ኦፐሬሽን መምሪያ ሃላፊ | ኮ/ል | ወዲ ጠውቅ | ትግሬ |
| 24 | እቅድ ዝግጅትና ፕሮግራም መምሪያ ሃላፊ | ኮ/ል | ተክላይ አሸብር | ትግሬ |
| 25 | መከላከያ ኢንዱስትሪዎች ማስትባበሪያ ሃላፊ | ኮ/ል | ወዲ ነጋሽ | ትግሬ |
| 26 | መከላከያ ፋይናንስ መምሪያ ሃላፊ | ኮ/ል | ዘውዱ | ትግሬ |
| 27 | መከላከያ ግዥ መምሪያ ሃላፊ | ኮ/ል | ግደይ | ትግሬ |
| 28 | መከላከያ በጀት መምሪያ ሃላፊ | አቶ | ብርሃነ | ትግሬ |

## በመከላከያ ሰራዊ ውስጥ ባሉ ቁልፍ የአዛዥነት ቦታዎች ላይ የሚገኙ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች .. . . (ከገጽ 3 የዞረ)

**አጭር ማጠቃለያ**

1. በሃገሪቱ -ውስጥ ባሉት 61 ቁልፍ የመከላከያ ሃላፊነቶች ከተመደቡት ግለሰቦች መሃል በዘውግ ተዋጽአዋቸው

- 57 ትግሬዎች
- 2 አገዎች
- 2 አማሮች ይገኙበታል

2. ከላይ የተቀመጠው አሃዝ የበለጠ ሲተነትን

- በመከላከያ ውስጥ የሚገኙ 7 ቁለፍ ቦታዎች 6 መምሪያዎቸና የኤታማዡር ሹምነቱን ጨምሮ በሙሉ የተያዙት በትግሬዎች ነው
- ከእዚህ በተጨማሪ በመከላከያ ሃይሉ ውሰጥ የሚገኙ 28 የጦር አዛዦች መሃል 26ቱ ትግሬዎች ሲሆኑ የተቀሩት ሁለቱ አገዎች ናቸው። በደረሰን መረጃ መሰረት ሁለቱም አገዎች ለስም የተቀመጡ ሲሆኑ ማንኛውም ሰልጣን ያለው በስራቸው ባሉ የትግራይ መኮንኖች ፈላጭ ቆራጭንት የሚፈጸም ነው። ይህ አሰራር የትግራይ ተወላጆች በሃላፊነት ባለተመድቡባቸው ቦታዎች በሙሉ በስራ ላይ የዋለ ነው። በሰራዊቱ ውስጥ አልፎ አልፎ በተለያዩ ቦታዎች በሃላፊነት የተመደቡ ጥቂት የትግራይ ተወላጆች ያልሆኑ ቢገኙም አንዳቸውም ስልጣን የሌላቸው በስራቸው በተመደቡ ትግሬዎች የሚታዘዙ ናቸው
- ከላይ ከተጠቀሱት 61 ከፍተኛ ቁልፍ ሃላፊነቶች መሃል በአጠቃላይ 25 ጄነራሎች ሲገኙ ከእነዚሀ መሃል 22 ትግሬዎች ሲሆኑ 2 አማራዎች 1 አገው ይገኙበታል።
- ከሁሉ የሚገርመው ከላይ ከተጠቀሱት ቁልፍ 61 የሃላፊነት ቦታዎች ላይ ለይስሙላ እንክዋን ቢሆን አንድም የኦሮሞ ተወላጅ አለመገኘቱ ነው። ይህ በወታደራዊ ዘረፉ ከፍተኛ ዘረኛነት የሚንጸባረቅበት አሰራር በሲቪል አስትዳደሩና መንግስታዊ በሆኑ ተቅዋማት በሙሉ የሚታይ ነው። በእዚህ በዘረኛነት መጠቃቀም በሚያዝ ስልጣን በመጠቀም በተለያዩ ሃላፊነቶች ላይ የተቀመጡት የትግራይ ተውላጆች በሙስናና እንዳሻችው ራሳችው ለመጠቀም በሚያወጡት መመሪያ አማካይነት የከፍተኛ ሃብት ባለቤቶች ሆነዋል።
- ከእዚህ በተጨማሪ አሁን በስልጣንና በስራ ላይ ከሚገኙት 39 ጄነራሎች መሃል 28ቱ ትግሬዎች ሲሆኑ 5 ኦሮሞ 4 አገው 2 አማሮች ይገኙበታል። ቀደም ብለን እንደጠቀስነው አምስቱም የኦሮሞ ጄነራሎች ምንም ሃላፊነት በሌለው ቦታ የተመደቡ ናቸው። የጀነራሎቸ ሹመት የፖለቲካ ሹመት ሲሆን ሹምት ስጭው መለስ ዜናዊ ለብሄራዊ ተዋጽኦ ተጨንቆ የሚፈጽመው መሆኑን ስንስማ ይህ ጭንቀት በሌለበት ከጄነራልነት በታች ለሚገኙ ማእረጎች የሚስጥ ሹምት ምን ያህል በዘረኛነት የተጨማልቀ አንደሚሆን ማሰቡ የሚሰቀጥጥ ይሆናል።
- አሁን በስራዊቱ ውስጥ ያለው ዘረኛ አደረጃጀት ቀድሞ ከነበረበት አስከፊ ደረጃ አሁን ወደሚገኘበት የባሰ ደረጃ የደረስው ከምረጫ 97 በሁዋላ ነው። በአስር ሽዎች የሚቆጠሩ የአማራና የኦሮሞ ተወላጆች ለህገ መንግስቱ ታማኝ አይደላችሁም በሚል ሰበብ በጅጅጋ (2800) በሃረር(1800) በውርሶ፣ ብላቴ፣ አዋሳ፣ ታጠቅ፣ ጦላይ፣ ደዴሳ፣ ብር ሸለቆ፣ ፓዊ፣ አዘዞ፣ ጢጣ (ደሴ)፣ ሽሬ፣ ኩያ፣ አዋሽ አርባ( 520) ሰመራ በተባሉት ቦታዎች ታስረው ከ4 ወር እስከ 17 ወር ከተንገላቱ ብሁዋላ የጡረታ መብታቸው እንክዋን ሳይጠበቅ፣ ወደ ትውልድ ሃገራቸው መሳፈሪያ ሳይሰጣቸው ከሰራዊቱ ተባረዋል። ይህ በማእከል የሚታውቁ እስር ቤቶች ሲሆኑ በየከፍለ ጦሩና በየሻለቃው የታሰሩና የትስቃዩ በርካታ ወታደሮች እንደነበሩ ይታወቃል። የታሰሩትና የተባረሩት ከኮነኔል አንስቶ እስከ ተራ ወታደር የሚያካትት ሲሆን የተባረሩት ጄነራሎችንም ይጨምራል። ዛሬ ከመቼውም በላይ አይኑን አፍጦ የምናየው ዘረኛነት የእዚህ በዘር ላይ ያነጣጠር በሰራዊቱ ወሰጥ የተሰራ የዘር ማጽዳት ስራ ነው።
- ይህ ዘረኛ አስራር በፖሊሱና በደህንነት ሃይሉ ውስጥ ስንመለከተው የምናገኘው ጭብጥ ከስራዊቱ የከፋ ነው።
- የሃገሪቱ ሃብት በዘረኛ ዘረፋ ምን ያህል እንድሚዘረፍ በእዚህ ላይ ደምረን ስንመልከተው እውን ኢትዮጵያ በኢትዮጵያውያን እጀ ወይንስ በባእድ ወራሪዎች እጅ የሚያስኝ ጥያቄ የሚያስንሳ ነው
- ይህ የማያስቆጣን ከሆነ ሌላ ምን ሊያስቆጣን ይችላል። ከዚህ በላይ የግልና የሃገር ውርደትና ሞት ይኖራል ወይ?

## ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ በአውሮፓ ከተማዎች እየተዘዋወሩ ህዝባዊ ስብሰባዎችን ማድረግ እና ባለስልጣናትን ማናገራቸውን ቀጥለዋል (ከገጽ 1 የዞረ)

የስብሰባውን አዳራሽ ሞልተውት የነበሩት ኢትዮጵያውያን ከስድስት ሰዓት ውይይት በኋላ ሲወጡ ብዙዎች ከመቼውም በበለጠ መልኩ ትግሉን እንደሚረዱ ቃል መግባታችውን ዘጋቢያችን ገልጿል። በስብሰባው ላይ እና በኋላም ለንቅናቄው ማጠናከሪያ እንዲሆን በጨረታ እና በምግብ ሽያጭ በተደረገ የገንዘብ ማሰባሰብ ሂደት ከተገመተው በላይ ገቢ መሰብሰቡ ተያይዞ በመጣ ዘገባ ተገልጿል።

ቀጥሎም እሁድ ግንቦት 16 ቀን በስዊዘርላንድ በተደረገው ህዝባዊ ስብሰባ በርካታ ኢትዮጵያውያን በተገኙበት ገንቢ ውይይት እንደተደረገና ስኬታማ የገንዘብ ማሰባሰብ ሂደት እንደተካሄደም ዘጋቢያችን ከስፍራው ዘግቧል። በስፍራው የተገኙትን ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ተነሳሽነት በሚያሳይ መልኩ፣ ባለፈው ሳምንት ስዊድን አገር ስቶክሆልም ከተማ እንደተደረገው ሁሉ አንድ የኢትዮጵያ ባንዲራ ያለበት የግንቦት 7 አርማ ሶስት ሺህ ዶላር መሸጡን ዘጋቢያችን አያይዞ ጠቅሷል።

ዶ/ር ብርሃኑ በየሄዱባቸው አገራት ካሉ ባልስልጣናት ጋርም በመገናኘት ውይይቶችን እያደረጉ ሲሆን፣ ከጀርመን ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከፓርላማው ጋር ባደረጉት ውይይት፣ በኢትዮጵያ ስላለው አፈናና ጭቆና፣ ሰላማዊ ትግል ከ97ቱ ምርጫ በኋላ ከመቀልበሱ የተነሳ ኢትዮጵያኖች መብታቸውን ለማስከበር ሲሉ ሁለገብ ትግልን ለምን እንደመረጡ አስረድተዋል። ጨምረውም፥ የምእራብ አገሮች በኢትዮጵያ ውስጥ ሊፈጠር ከሚችለው ዲሞክራሲ የበለጠ መረጋጋት እና ልማት እንደሚገኝ እና ይህም ለአጭር እና ለረጅም ጊዜ ጥቅማቸው የሚበጅ መሆኑን ገልጸውላቸዋል። ዶ/ር ብርሃኑ በአፍሪቃ ቀንድ አካባቢ ላለው መረጋጋትም ሆነ ለአለም ደህነንት ያሳስበናል ለሚሉት የምእራቡ አገራት በኢትዮጵያ ውስጥ ለዴሞክራሲ የሚካሄደውን ትግል መደገፍ ከዘላቂ ጥቅማቸው ጋር የተያያዘ መሆኑን እንዲረዱ አድርገዋል።

ዶ/ር ብርሃኑ በተያዘላቸው የግዜ ሰሌዳ መሰረት ወደ ቀጣዩ አገር ያቀኑ ሲሆን፣ በሚቀጥለው ቅዳሜ በሆላንድ አገር በአምስተርዳም እና የጉብኝታቸውን የመጨረሻ ስብሰባ፣ በእንግሊዝ ዋና ከተማ በለንደን እንደሚያደርጉ ታውቋል።

## በግንቦት 7 ንቅናቄ የተደናበረው የወያኔ አገዛዝ ጎረቤት አገር በስደት የሚገኙትን ሳይቀር መወንጀል ጀምሮአል (ከገጽ 1 የዞረ)

ወያኔ በወገን እና በሀገር ላይ የሚፈጽመው ቅጥ ያጣ ግፍ እንደ እግር እሳት እንደሚለበልባቸው የተናገሩት አንድ ስደተኛ አብዛኛው በጎረቤት እና በአካባቢው ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮድያዊያን የሚጠብቁት የግንቦት ሰባትን የክተት ጥሪ እንደሆነ ተናግረዋል። እኛ ኢትዮድያዊያን በአለም ከምንታወቅባቸው ነገሮች አንዱ ለራሳችን ግለሰባዊ ክብር እና ለማንነታችን በምንሰጠው ከፍ ያለ ዋጋ ነው ያሉት እኚሁ ግለሰብ፣ ወያኔ ደግሞ እያንዳንዳችንን እንደወራሪ ሰራዊት በእናት አባቶቻችን ፊት፣ በሚስት በልጆቻችን ፊት አዋርዶናል፤ የውርደቱም መጠን ጥልቅ ነው” ሲሉ ምሬታቸውን ገልጸዋል።

ሌላው በካምፓላ በስደት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን “አብዛኞቻችን ባለን የፓለቲካ አስተሳሰብ ብቻ ከእናት ሀገራችን ተሰደን ካለ ሀገር እንድንኖር የተፈረደብን ስደተኞች ነን። የጄኔቫ የስደተኞች ኮንቬንሽን በሁለተኛ ወይም በሶስተኛ ሀገር ዋስትናችን ተጠብቆ የመኖር የማይገሰስ መብት አጎናጽፎናል። በታወቁ የሰብአዊ መብት ተማጋቾች እና የዘር ፍጅት ተከላካዮች ክስ የሚቀርብበት እንደ መለስ ያለ ኋላቀር እና ዘረኛ አምባገነን በፈለገው ጊዜ መብታችንን ሊገፍ አይችልም። እዚህ ያለን ሀገር ወዳድ ኢትዮድያዊያን ሀገራችንን ለመታደግ እና ማንኛውንም መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ እንደሆንን እንዲታወቅ እንፈልጋለን” ሲሉ አስተያየታቸውን አጠቃለዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ** እና **በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org